የሰበር መ/ቁ.15531

የካቲት 6/99 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
2. ” አሰግድ ጋሻው
3. ” መስፍን ዕቁበዮናስ
4. ወ/ት ሂሩት መለሠ
5. አቶ ተሻገር ገ/ሥላሴ

አመልካች፡- የኢት/ኤሌክትሪክ ኃ/ኰ/ነ/ፈጅ እመቤት ለማ ቀረበች

መልስ ሰጭ፡- አቶ አዱኛ ገመዳ ቀረበ

## ፍ ር ድ

በዚህ ጉዳይ ለሰበር ችሎት የቀረበው ክርክር የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድን ስልጣን የሚመለከት ነው፡፡

በመ/ሰጭ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ክሱ የቀረበው ደረጃዬ ዝቅ ተደርጓል በሚል ነው፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ አሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክሱን ለማየት ስልጣን አለው በማለት የተሰጠ ነው፡፡ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት መ/ሰጭ መልሱን አቅርቧል፡፡

ችሎቱም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የሚታዩ የስራ ክርክሮች ምን አይነቶች ናቸው የሚለውን የሕግ ነጥብ መሰረት በማድረግ አቤቱታ የቀረበለትን ውሣኔ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

ይህ ችሎት በመ/ቁ. 18180 አግባብነት ያላቸውን የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎች በመተርጎም የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የማየት ስልጣን የተሰጠው የወል የስራ ክርክር ጉዳዩችን ነው፣ አንድ የስራ ክርክር የወል የስራ ክርክር ነው የሚባለው ጉዳዩ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው፤ በአንፃሩ አንድ የስራ ክርክር የወል ሣይሆን የግል የስራ ክርክር ጉዳይ ነው የሚባለው የክርክሩ ውጤት በተከራካሪው ሰራተኛ (ሰራተኞች) ላይ ብቻ ተወስኖ የሚቀርብ ሆኖ ሲገኝ ነው በማለት የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

መ/ሰጭ በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ደረጃዬ ዝቅ ተደርጓል በሚል ያቀረበው ክስ የጋራ በሆነ የሰራተኞች መብትና ጥቅም ላይ አሉታዊም ሆነ አወንታዊ ውጤት የሚያስከትል ባለመሆኑ የወል የስራ ክርክር አይደለም በመሆኑም ጉዳዩን ለማየት የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ስልጣን ያለው ባለመሆኑ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

የምዕ/ኦሮሚያ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ.ቁ. ታህሣሥ 25/1995 የሰጠው ውሣኔና ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ. 00692 በ21/7/96 የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

- ግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡



የሰ/መ/ቁ. 21730

11/7/99

ዳኞች፡- 1. አቶ ፍስሐ ወርቅነህ
2. አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
3. አቶ ጌታቸው ምህረቱ
4. አቶ መስፍን እቁበዮናስ
5. ወ/ት ሒሩት መለሠ

**አመልካች፡-** ፍሬህይወት እርቂ

**ተጠሪ፡-** የኢት. ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን

*የስራ ክርክር - ህግ ወጥ የስራ ውል ማቋረጥ - ወደ ስራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሰራተኛ የሚከፈለው ውዝፍ ደሞዝ - አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43(5)*

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ከስራ የተሰናበቱት በህገ ወጥ መንገድ ስለሆነ ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል ሲሉ ቢወስኑም ውዝፍ ደሞዝን በተመለከተ ሳይወስኑ በዝምታ በማለፋቸው የቀረበ አቤቱታ ነው፡፡

**ውሣኔ፡ -** የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃና ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡና ውሳኔ ተሻሽሎ ተጠሪ የዘጠኝ ወር ከ23 ቀን ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈላቸውና ሌሎች ወጪና ኪሳራዎች እንደመሰለው እንዲወስን ጉዳዩ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ ተወስኗል፡፡

1. የስራ ውሉ በሕገ ወጥ መንገድ የተቋረጠና ወደ ስራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት ከስድስት ወር የማይበልጥ ደሞዝ ሊወሰንለት ይገባል፡፡
2. ጉዳዩ በይግባኝ ታይቶ የሰራተኛው መመለስ ውሳኔ ከፀና ከአንድ አመት ያልበለጠ ውዝፍ ደሞዝ ፍርድ ቤቱ ሊወሰንለት ይገባል፡፡